# የቀድሞው ቅንጅት አመራር ህሊናዊነት የተፈተሸበት አንድ ጥሩ አጋጣሚ

*(የውይይት መነሻ ሀሳብ፤ በሔኖክ ሄደቶ)*

ብዙ ኢትዮጵያውያን የቀድሞው ቅንጅት በእንደዚህ ማለቂያ የለሽ የመከፋፈል ሂደት ውስጥ የመግባቱ እውነት ያልተጠበቀና ፍፁም አስደንጋጭ፣ አለፍ ሲልም ተስፋ አስቆራጭ ሆኖባቸው ይታያል። በተፈጠረ ጥቂት ወራት ውስጥ ባገኘው ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍና የፓርላማ ወንበር ብዛት ሰክሮ ቀጥ ብሎ በሁለት እግሮቹ ወደፊት መራመድ ቸግሮት ተወለካክፎ ከተማሰለት ጉድጓድ ውስጥ የገባው ቅንጅት ከወደቀበት ተፍጨርጭሮ ከመነሳት ፈንታ የጀመረውን የቁልቁለት ጉዞ ሊገፋበት ስለምን እንደወደደ ለብዙወች ግራ እንደገባቸው ነው። የቀድሞው ቅንጅት አመራር አባላቱንና ደጋፊዎቹን በአንድነት አሰባስቦ ሰላማዊ ትግሉን ከመቀጠል ይልቅ እንደ አሜባ አይነት የሁለትዮሽ የመራባት ሂደት (binary reproductive system) ከሁለት ቦታ እራሱን እየከፋፈለ ወደ ብዙ ትንንሽ ስብስቦች እና ተናጠል ፖለቲከኞች የመበታተኑ ነገር በእርግጥም ለውጪ ተመልካች እንቆቅልሽ ቢሆን አይገርምም።

የእንቆቅልሹን ፍቺ ለማግኘት ብዙ መማስን አያስፈልግም ።የሚያስፈልጎት ነገር ቢኖር አንድ ከፍተኛ ግምት የሰጡት ሰው ያልጠበቁት አይነት ቅለት ሲያዩበት ሊያጋጥም የሚችለው አይነት የቅርታ እና ተስፋ መቁርጥ ስሜት ብዙ ጉዳት እንዳያደርስቦት ተጠንቅቀው የአመራሩን ቡድናዊ እና ግለሰባዊ ባህሪያት በመጠኑ መመርመር ነው።

ይህን ለማድረግ እንዲረዳዎ ለዛሬ የምርጫ ዘመቻው ከመጀመሩ በፊት ያጋጠመን አንድ አስቸጋሪ ጉዳይ ሙሉ ይዘት አቅርቤሎታለሁ። አከራካሪው ጉዳይ በወቅቱ አንዱ የቅንጅት አባል ፓርቲ የነበረው ኢዴአፓ-መድህን (አሁን ኢዴፓ) ያቀረበው ቅንጅቱ በዚያ ምርጫ አገኘዋለሁ ብሎ የሚያስበውን ከፍተኛ ውጤት ቀድሞ እንዲገምት እና የምርጫ ዘመቻውም በእቅዱ መሰረት እንዲቃኝ የሚጠይቅ ነበር። በአጀንዳው ዙሪያ ውይይት ሲጀመር የቅንጅቱን አመራር ቡድናዊ እና ግላዊ ባህሪያት ፍንትው አድርገው ሊያሳዩ የሚችሉ ሁለት ጎራዎች ተፈጠሩ። አንደኛው ጎራ በወቅቱ የመኢአድ እና ቅንጅት ሊቀመንበር በነበሩት በአቶ ኃይሉ ሻውል የሚመራ እና አቋሙም "በምርጫው አሸንፈን የመንግስት ስልጣን እንረከባለን" የሚል ሲሆን ሁለተኛው እና በወቅቱ የኢዴአፓ-መድህን ዋን ፀሀፊ እና የቅንጅቱ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ በነበሩት በአቶ ልደቱ አያሌው የሚመራው ጎራ ደግሞ አቋሙ "በዚህ ምርጫ ልናሸንፍ የምንችለው በቂ የሚባል (ከመቶ ያልበለጠ) የፓርላማ ወንበር እና አዲስ አበባ ከተማን ብቻ ነው" የሚል ነበር። የዚህ ክርክር ፍሬ ሀሳብ ቡድኖቹ ስለምርጫው የነበራቸውን እይታ ከማሳየትም አልፎ ለተነሳንለት የቅንጅቱን አመራር ፖለቲካዊ ባህሪያት የመመርመር ሀሳብ ትልቅ ግብአት ሊሆን የሚችል በመሆኑ እንዳለ ቀርቧል። ፅሁፎቹን በጥሞና አንብቦ ሀሳብ መሰንዘር በጣም ጠቃሚ ይሆናል። ***የቅንጅቱ አመራር በአቶ ኃይሉ የቀረበው መከራከሪያ "አሳምኖኛል፤ እቅዴም ይኸው ነው!" በሚል የተቀበለው መሆኑን ያጤኗል። በቅድሚያ የአቶ ኃይሉን ጽሁፍ እንሆ!***

## <u>የቅንጅት የአጭር ጊዜ አመልካች እቅድ</u>

*መግቢያ፡-* ቅንጅት ከመመስረቱም በፊት አባል ድርጅቶች ባካሔዱት የማደራጀት ስራና ቅንጅቱም በተፋጠነ ሁኔታ እራሱን ከህዝብ ጋር በማስተዋወቁ የማሸነፍ እድሉ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ነው። ይህ እድል በዚህ በአሁኑ ምርጫ ካልተጠቀመበት ለረጅም ጊዜ

የሚከማች እሴት እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን። ፖለቲካ ተለዋዋጭ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ መስዋእትነት የከፈሉት በገኘው ፓርቲ እንደሚለቀሙ መገንዘብ አለብን።

ከዚህም በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ ገጠሬው ለረጅም ጊዜ የመንግሥት ለውጥ ጠብቋል። በትእግስት የጠበቀው የግንቦቱ 1997 ምርጫ ሰላማዊ ለውጥ ያመጣል ብለን እንዲታገል ስለጠየቅነው ነው። ስለዚህ ይህ ምርጫ ቢጭበረበር ወይም በቅንጅቱ ድክመት ባይሳካ በሰላም እንድንቀጥል ሕዝብ ይፈቅዳል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው። በቅንጅት ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በምሁሩ ላይ የሚኖረው እምነት ከናካቴው እንዳይዳፈን ሥጋት ሊኖር ይገባል።

## <u>የተመራጭ አቀራረብ</u>፤

ውሳኔ ከማሰብ አስቀድሞ የቅንጅቱን ተመራጭ ስርጭት መመልከቱ ይጠቅማል በሚል ከዚህ በታች በክልል ሰፍሯል።

| ተ.ቁ | ክልል | ለተወካዩች ም/ቤት | | ለክልል ም/ቤቶች | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቅንጅት የቀረቡ | ለማሸነፍ የተገመተ | ጠቅላላ በቅንጅት የቀረበ | የማሸነፍ ግምት |
| 1 | አ/አበባ | 23 | 16 | 137 | 95 |
| 2 | አማራ | 136 | 95 | 275 | 180 |
| 3 | አፋር | 8 | 6 | 61 | 45 |
| 4 | ደቡብ | 119 | 95 | 303 | 210 |
| 5 | ኦሮሚያ | 148 | 74 | 275 | 110 |
| 6 | ትግራይ | 23 | 8 | - | - |
| 7 | ሌሎች | 11 | 6 | - | - |

የማሸነፍ ግምት የተወሰደው በሚከተሉት ታሳቢዎች ነው።

1. እስከዛሬ ሲደረግ የነበረው የማደራጀት ሥራ ስፋትና ጥልቀት፤
2. በየአካባቢውና በአጠቃላይ ስብሰባዎች የሕዝብን አስተያየት በመታዘብ፤
3. ቅንጅቱን የሚወዳደሩ ፓርቲዎች ጥንካሬና በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት በመገመት፤

ስለዚህ የሚከተሉት ውጤት ይገኛል ብለን መገመት እንችላለን።

(ሀ) የሕዝብ ተወካዩች ም/ቤት 290 (51%) መቀመጫዎች በማግኘት የፌዴራል መንግስት መረከብ፤
(ለ) በአዲስ አበባ ክልል 95 መቀመጫዎች (70%) በማሸነፍ የከተማውን አመራር መያዝ፤
(ሐ) በአማራው ክልል190 መቀመጫዎች (61%) በመያዝ ክልልን አስተዳደሩን መረከብ፤
(መ) በደቡብ ክልል 210 መቀመጫዎች (61%) ማግኘትና አስተዳደሩን መረከብ፤
(ሠ) በአፋር ክልል 45 መቀመጫዎች (70%) በማግኘት አስተዳደሩን መረከብ፤

*በመቀጠል የአቶ ልደቱን ትንታኔ እንመልከት።*

## ለቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ምክር ቤት የምርጫ ስትራቴጂን አስመልክቶ በአማራጭነት ለውይይት የቀረበ መነሻ ሃሣብ

በአሁኑ ወቅት በቅንጅቱ አባል ድርጅቶች ወይም በአመራር አባላቱ መካከል በመጪው ምርጫ ቅንጅቱ ሊያገኝ ስለሚችለው ውጤት ሁለት የተለያዩ ሃሣቦች አሉ። አንዱ በመጪው ምርጫ ከ50% በላይ የፓርላማ መቀመጫ በማሸነፍ የመንግስት ሥልጣን እንይዛለን የሚል ሲሆን ሁለተኛው የምናገኘው ውጤት በፓርላማ በቂ የሚባል ውክልና ከማግኘትና የአዲስ አበባ ምክር ቤትን አሸንፈን ከመቆጣጠር ያለፈ አይሆንም የሚል ነው። በእኔ በኩል የምስማማው በሁለተኛው ሀሳብ ስለሆነ ሀሳቤን አሳማኝ ያደርጋሉ ብዬ የማምንባቸውን ነጥቦች ለመግለፅ ልሞክር።

### 1. በሁለቱ ሃሳቦች ዙሪያ የመወያየቱ አስፈላጊነት፣

እንደ አንድ የፖለቲካ አመራር አካል ከምርጫው ፍፃሜ በፊት በእነዚህ ሁለት የተለያዩ ሃሳቦች ዙሪያ በቂ ውይይት አድርጎ የቅንጅቱ ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ወደትክክለኛው ግምት መድረስ ትክክለኛውን የምርጫ ዘመቻ እስትራቴጂ እንድንከተል ስለሚያደርገን አስፈላጊ ነው። ይኸውም፣ የቅንጅቱ ውጤት አሸንፎ የመንግስት ስልጣንን መጨበጥ ከሆነ ቅንጅቱ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚያስችለውን የፖሊሲ የመዋቅርና የሰው ኀይል ምደባ ዝግጅት ከወዲሁ ሌት ከቀን ሠርቶ ማጠናቀቅ ይገባዋል። ውጤቱ የመንግስት ስልጣን ከመጨበጥ በመለስ በቂ የፓርላማ ውክልና ማግኘትና የአ/አበባ ምክር ቤትን ማሸነፍ ከሆነም ዞሮ ዞሮ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን በምርጫ ዘመቻችን ሙሉ ሂደት ህዝብን የምንቀሰቅሰው በምርጨው እንደምናሸንፍ እርግጠኞች እንደሆን አድርገን ስለሆነ ከምርጫው በኂላ ሳናሸንፍ የቀረንበትን በቂ ምክንያት ለህዝብ ማቅረብ የምንችልበትን ስልት ከወዲሁ ማመቻቸት ይኖርብናል። ከዚህ በተጨማሪ የአ/አበባ መስተዳድርን በበላይነት ይዘን ለማስተዳደር የሚያስቸለንን ሁለንተናዊ ቅድመ ዝግጅትም ከምርጫው ፍፃሜ በፊት ማከናወን ይጠበቅብናል። ሌላው በነዚህ ሁለት አከራካሪ ሀሳቦች ላይ ተወያይቶ መተማመን ላይ መድረስ የሚያስገኘው ጥቅም ቅንጅቱ ያለውን ውስን የሰው፣ ሐይል፣ ጊዜና ገንዘብ ውጤታማ እንደሚሆን አስቀድሞ በታወቀ የስራ ተግባር ላይ ለማዋል ስለሚያስቸለው ነው።

### 2. የመንግስት ስልጣን ለመያዝ በሚያስችል መጠን ማሸነፍ አንችልም የምንልበት መነሻ ምክንያቶች

የመጀመሪያው ምክንያት ቅንጅታችን መላውን ሀገሪቱንና አብዛኛውን ህዝብ በሸፈነ መጠን ውጤታማ የምርጫ ዘመቻ ለማካሄድ የሚያስችል ሪሶርስና መዋቅራዊ ዝግጅት የለውም የሚል ነው። በዚህ ምርጫ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት 75% ማሀይም የሆነውንና የመገናኛ ብዙሀን ተጠቃሚ ያልሆነውን ህዝብ በየቤቱ እየደረሱ ስለቅንጅቱ ማንነት አላማና ስለምርጫው አፈፃፀም በቂ የሆነ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ በያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የስርዓቱን የማጭበርበሪያ ስልቶች በሚገባ ተገንዝበው የምርጫውን ሂደት በንቃት በመታዘብ ውጤታችንን እንዳንቀማ የሚያደርጉ በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ብቁና ታማኝ ታዛቢዎች ያስፈልጉናል። እነዚህን ሁለት መሰረታዊ ተግባራት በብቃት ለማከናወን አሁን ያለን ጊዜ፣ ገንዘብ፣ የሰው ሐይልና በአጠቃላይም ድርጅታዊ አቅም የሚያስችለን አይደለም።

ሁለተኛው ምክንያት ከቅንጅታችን አቅም ጋር ሲነፃፀር ገዢው ፓርቲ ባሁኑ ወቅት የተሻለ ድርጅታዊ አቅምና ሪሶርስ አለው የሚል ነው። ሁሉም እስከቀበሌ ድረስ ያሉ

መንግስታዊ መዋቅሮች በገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ስር ያሉ በመሆኑ ገዢው ፓርቲ በቀላሉ ከያንዳንዱ ዜጋ ጋር ተገናኝቶ የራሱን አጀንዳ ለማስፈፀም የሚያስችለው ድርጅታዊ መዋቅርና አቅም አለው። ገዢው ፓርቲ ሁሉንም አይነት መገናኛ ብዙሀን እንደልቡ ለመጠቀም ያለው እድል፣ በህዝብ ውስጥ አሁን ብቃት ያለው ፓለቲካዊ ተሳትፎ ለማድረግ ያለው የፍርሀት ድባብ፣ አብዛኛው ህዝብ ስለምርጫ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ፣ የአብዛኛው ህዝብ የኑሮ መሰረት ማለትም መሬት፣ የኪራይ ቤት፣ የመንግስት ሥራ፣ የማደበሪያና የብድር አቅርቦት የመሳሰሉት በገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ስር መሆናቸው የምርጫውን ውጤት የተዛባ ለማድረግ እገዛ የሚያደርጉለት ሁኔታዎች ናቸው። ገዥው ፓርቲ እኛ በብቃት በማንሸፍናቸው በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያዎች ካድሬዎቹን አሠማርቶ ሕዝቡን ለማጭበርበርና ለማፈን የሚያስችል በቂ መዋቅራዊ ዝግጅት አለው።

ሦስተኛው ምክንያት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ምርጫውን እንዲያስፈፅሙ የተቀመጡት የምርጫ ቦርድ ሠራተኞች የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች መሆናቸው ነው። አስፈፃሚ አካሉ ብቻ ሳይሆን ምርጫውን ለመታዘብ በሕዝብ ታዛቢነት ስምና በሞያ ማህበራት ስም የሚሰማሩት አብዛኛዎቹ ታዛቢዎች ከኢህአዴግ ጋር ልዩ ግንኙነት ያላቸው ስለሆኑ ለገዥው  ፓርቲ የአፈናና የማጭበርበር ስልት አመቺ የሆኑ  ሁኔታዎች የእኛ አቅም ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ አስቀድመው ተዘርግተዋል። በመራጮች ምዝገባ ወቅትም በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ለ45 ቀናት ቋሚ ታዛቢዎች አስቀምጠን መቆጣጠር ባለመቻላችን ገዥው ፓርቲ ጠንካራ ፉክክር ይገጥመኛል ብሎ በገመተባቸው የምርጫ ክልሎች ከፊሉን የማጭበርበር ስራ አስቀድሞ አከናውኖታል ።

አራተኛው ምክንያት ገዥው ፓርቲ በነፃና ፍትሀዊ ምርጫ ስልጣኑን ለማስረከብ ገና የባህሪና የአስተሳሰብ ለውጥ አላመጣም ። የአካባቢያችንና የአለም አቀፍ ሚዛንም በገዥው ፓርቲ ላይ ከፍተኛ ዲፕሎማሳዊ ጫና ለመፍጠር የሚያስችልና በአንፃሩ ተቃዎሚ ፓርቲዎችን በርግጠኝነት ለመደገፍ የሚያስችል ነው ብሎ ለመተማመን የሚያበቃ አይደለም ። የሀገሪቱ መከላከያ፣ ፓሊስና ደህንነት ሀይል በገዥው ፓርቲ ጥብቅ ቁጥጥር ባሉበት ሁኔታ፣ ስርአቱ ሰላማዊ ሽግግርን ለማየት ባልተዘጋጀበትና አለማቀፍ ህብረተሰብም ተቃዋሚዎች በኢትዩጵያ የተሻለ ስርአት ይገነባሉ የሚል አስተማማኝ እምነት ፈጥሮ በማይታይበት በአሁኑ ወቅት ከላይ የተጠቀሱትን እንቅፋቶች በብቃት ተወጥቶ የአሸናፊነት ውጤት ማግኘት አስቸጋሪ ይመስለኛል።

አምስተኛው ምክንያት በዘንድሮ ምርጫ በርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የግል ተወዳዳሪዎች በአንድ ምርጫ ክልል ተደራርበው ገብተዋል። ሕዝብ በአንድ በኩል በተቃዋሚዎች መካከል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተቃዋሚዎችና በግል እጩዎች መካከል ያለውን ያስተሳሰብና የአላማ ልዩነት ጊዜና ድፍረት አግኝተን በውል ባላስጨበጥነው ባሁኑ ወቅት በተቃዋሚው ጎራ የሚሰጠው ድምፅ ስለሚከፋፈል ገዥው ፓርቲ በአነስተኛ ድምፅ የማሸነፍ እድሉ የሰፋ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንዳንዶቹ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ ድርጅቶችም ቅንጅቱን ከኢህአዴግ ባላነሰ መጠን ለራሳቸው ህልውና አደገኛ አድርገው ስለሚመለከቱ ቅንጅቱ እንዳያሸንፍ ውስጥ ውስጡን ጥረት ማድረጋቸው ስለማይቀር የቅንጅቱን የማሸነፍ አቅም በመሸርሸር ረገድ የማይናቅ ሚና ይኖራቸዋል። በአሁኑ ወቅትም ይህንን ስጋት የሚያጠናክሩ መረጃዎች ከደቡብና ከኦሮሚያ አካባቢዎች እየደረሱን ነው። በተለይም በሀድያና ከንባታ አካባቢዎች በአንድ በኩል እራሳቸው ተቃዋሚዎች የቀኝ ሀይሎች ስብስብ የሆነውን ቅንጅትን ከምትመርጡ ኢህአዴግን ብትመርጡ ይሻላል በማለት በግልፅ መቀስቀስ መጀመራቸውን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ ከቻላችሁ እኔን ምረጡ ካልቻላችሁ ግን ያለፈውን ስርአት የሚመልስባችሁን ቅንጅትን ከመምረጥ ይልቅ ህብረቱን ምረጡ እያሉ እንደሚቀሰቅሱ

መረጃዎች እየደረሱን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለረጅም ጊዜ በተሰበከው የጎሳ ፓለቲካ ምክንያትም ሁኔታውን የሚለውጥ በቂ ፕሮፓጋንዳ መስራት እስካልተቻለ ድረስ ሰዎች በስማቸው የተደራጀ ድርጅት ለመምረጥ የሚኖራቸው ዝንባሌ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይሆንም፡፡

ስድስተኛው ምክንያት ቅንጅታችን በየአካባቢው ያቀረባቸው ከፊሉ እጩዎች የፓለቲካና የትምህርት ብቃታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ የእጩዎች ምልመላ በአብዛኛው በተጣበበ ጊዜ ውስጥ የተሰራ በመሆኑ ከእጩዎቻችን መካከል በህዝብ ዘንድ መልካም ስም የሌላቸውና የገዥው ፓርቲ ሰርጎ ገቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡መልካም ስም የሌላቸውን ሰዎች ገዥው ፓርቲ ሆን ብሎ እየተከታተለ በማጋለጥ የራሱን ፕሮፓጋንዳ ሊሰራ ስለሚችልና በሰርጎ ገብነት እራሳቸውን ያስገቡት ደግሞ እስከምርጫው ፍፃሜ ድረስ እየተንጠባጠቡ ከእጩነት በመውጣትና ልዩልዩ ድብቅ ተግባራትን በማከናወን የቅንጅቱን የማሸነፍ አቅም ማዳከማቸው አይቀርም፡፡ አንዳንዶቹ እጩዎች ደግሞ የረጅም ጊዜያት የትግል ተመክሮ የሌላቸው በመሆኑ በገዥው ፓርቲ ማስፈራራትና ልዩልዩ ተፅእኖዎች በቀላሉ እራሳቸውን ከእጩነት ሊያገሉ ወይም የምርጫ ቅስቀሳውን በሙሉ ልብ ላያካሂዱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በነዚህ አጠቃላይ ምክንያቶች ቅንጅታችን በዚህ ምርጫ አሸንፎ ይወጣል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ይመስለኛል፡፡

3. በቂ የፓርላማ መቀመጫ ማግኘትና አ/አበባ ምክር ቤትን ለማሸነፍ ይቻላል የምልበት መነሻ ምክንያት፣ በቂ የፓርላማ ውክልናም ሆነ የአዲስ አበባን ምክር ቤት ለማሸነፍ የሚያስችለን አንድ ዋና ምክንያት ነው፡፡ ይኸውም ከላይ የተዘረዘሩትን ተፅኖዎችና የአቅም ውስንነት ተቋቁመን የማሸነፍ እድል ያለን በከተሞች ነው የሚል ነው፡፡ ይኸውም፤

   3.1 አብዛኛው የተማረ ሕዝብ ማለትም የተሸለ የፓለቲካና የምርጫ ግንዛቤ ያለው የሚኖረው በከተሞች ስለሆነ፤

   3.2 የመገናኛ ብዙሃንን የማድመጥና የቅንጅቱን አማራጭነት የማወቅ እድል ያገኘው አብዛኛው ሕዝብ በከተማ ኗሪ ስለሆነ፤

   3.3 በከተሞች ምርጫውን በየጣቢያው ተገኝተው ሊታዘብልን የሚችሉ በቂ ቁጥርና ብቃት ያላቸው ታዛቢዎችን ቅንጅታችን ማቅረብ ስለሚችል፤

   3.4 ከተሞች ሕዝብ ተከማችቶ የሚኖርባቸው ጠባብ የምርጫ ክልሎች ስለሆኑ ቅንጅታችን በእያንዳንዱ ሰው ቤት በመድረስ እራሱን የማስተዋወቅና ስለምርጫው አፈፃፀም የማስረዳት አቅም ስለሚኖረው፤

   3.5 በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ ሕብረ-ብሔራዊ ይዘት ስላለው በብሔረሰብ ከተደራጁ ድርጅቶች ይልቅ ሕብረ-ብሔራዊ ድርጅቶችን የመምረጥ አዝማሚያ ስለሚኖረው፤

   3.6 የሀገር ውስጥና የውጭ ነፃ ታዛቢዎችና ነፃ ፕሬሶች በከተሞች በተሸለ ሁኔታ የምርጫውን ሂደት የመታዘብ እድል ስለሚኖራቸው፤

   3.7 በከተሞች ቅንጅታችን ያቀረባቸው እጩዎች በአንፃራዊነት አብዛኛዎቹ በፓርቲ ስራ ላይ በመቆየት ታማኝነታቸውን ያረጋገጡ፤ የተሸለ የትምርት ደረጃ ያላቸው፤ በስነ ምግናራቸውም የተሻሉ በመሆናቸው በከተሞች ቅንጅቱ የማሸነፍ እድሉ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

ስለዚህ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ50 ሺህ በላይ ሕዝብ የሚኖርባቸው የሀገሪቱ ከተሞች በሙሉ እንደ ቅንጅቱ ጠንካራ ይዞታ (strong hold) ሊታዩ ይችላሉ። የአዲስ አበባ መስተዳድር ምክር ቤት የሚቋቋመው ከአዲስ አበባ ከተማ ብቻ በሚመረጡ የክልል እጩዎች ስለሆነ በከተማዋ ሙሉ በሙሉ አሸናፊ በመሆን ወይንም አብላጫውን ድምፅ በማግኘት ምክር ቤቱን መቆጣጠር ይቻላል ብዬ አምናለሁ። በተመሣሣይ ሁኔታ በአድስ አበባ ከተማ ሙሉ በሙሉ ማሸረፍ ማለት 23 የፓርላማ መቀመጫዎችን ማሸነፍ በመሆኑ ቅንጅታችን በቀጥታ በፓርላማ ውስጥ አጀንዳ አስይዞ ለውይይት የማቅረብ እድሉን ያረጋግጣል ማለት ነው።

ከአዲስ አበባ ውጭ በበርካታ ከተሞች የማሸነፍ እድልም ስለሚኖው ቅንጅታችን በፓርላማ የሚኖረው ውክልና እስከ 87 መቀመጫ ወይም 16% ሊሆን ይችላል። ከከተሞች በተጨማሪ በአንዳንድ ሕዝብ እንደከተማ ተጠጋግቶ በሚኖርባቸው የደቡብ አካባቢዎች፣የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ ጠንካራ ድርጅታዊ ስራ በሠሩባቸውና ህብረተሰቡ ለየት ባለ ሁኔታ በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ምሬት በሚያሰማባቸው ጥቂት ልዩ አካባቢዎች ቅንጅታችን የማሸነፍ ተጨማሪ እድል ይኖረዋል። ነገር ግን በአንዳንድ ሥርዓቱ አስቀድሞ የማጭነርበር ስራ በሠራባቸው ከተሞችም ልንሸነፍ ስለምንችል በአጠቃላይ ለፓርላማ የምናሸንፈው ቁጥር ከላይ ከተጠቀሰው መጠን ብዙ ይርቃል ብዬ አልገምትም። በሀገራችን በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ 16% ብቻ በመሆኑ፣ከዚህም ውስጥ ከ50 ሺህ በላይ ሕዝብ የኒኖርባቸው ከተሞች 24 ብቻ በመሆናቸውና የነዚህ ከተሞች ሕዝብ ድርሻም 8% አካባቢ በመሆኑ ከከሞች ውጭ በሆኑ የተወሠኑ ቦታዎች ማሸነፍ ካልቻልን በፓርላማ የሚኖረን ውክልና የበለጠ ያነሥ ይሆናል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባው ቁም ነገር ይህንንም ውጤት ልናገኝ የምንችለው ሙሉ ትኩረታችንን፣ ጊዜያችንን፣ጉልበታችንንና ገንዘባችንን በእነዚህ ልናሸንፍ በምንችልባቸው አካባቢዎች ላይ በፍጥነት አሟጠን መጠቀም ስንችል ብቻ ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ያለንን ውስን አቅም በሀገር አቀፍ ደረጃ እናሸንፋለን ብለን በማሰብ ከበተነው የአድስ አበባ ምክር ቤትን ማሸነፍም ሆነ በፓርላማው ውስጥ በቂ የሚባል ወንበር ሣናገኝ ቀርተን በትግሉ የወደፊት እንቅስቃሴና በሕዝብ ሞራል ላይ ከፍተኛ አደጋ እንፈጥራለን የሚል ስጋት አለኝ።

## 4. የአዲስ አበባን ምክር ቤት ማሸነፍ እና በፓርላማ በቂ ውክልና ማግኘት ለወደፊቱ ትግላችን የሚኖረው ፋይዳ፣

በእኔ እምነት በዚህ ዓመት የአዲስ አበባ ምክር ቤትን ማሸነፍና በፓርላማ ውስጥ በቂ የሚባል ውክልና ማግኘት ግማሽ ኢትዮጲያን እንደመቆጣጠር የሚታይ ነው ብዬ አምናለሁ። ይህ እድልም በአምስት ዓመት በኋላ ህወሀት/ኢህአዴግን በአስተማማኝ ሁኔታ አሸንፈን የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ አስተማማኝ መሠረት ሆኖ ያገለግለናል ብዬ እገምታለሁ። ይህንን የምልበት ምክንያት-

4.1 ዘጠና በመቶ የሚሆነው የሀገራችን የተማረ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅም የሚገኘው በአዲስ አበባ ከተማ ነው። አዲስ አበባ ከተማን አሸንፈን ስንቆጣጠር እነዚህን ሪሶርሶች በመጠቀም ለመጭው አምስት ዓመት ምርጫ በቂ ድርጅታዊ ዝግጅፈት እንዲኖረን ያስችለናል።

4.2 አዲስ አበባ ከተማ በተጠቀሰው ምክንያት በሀገራችን ርዕሰ ከተማና የፖለቲካ እንቅስቃሴ መናሀሪያ በመሆንዋ የሥርዓቱን ድክመቶችና ስህተቶች ይበልጥ እያጋለጥን ሕዝቡን በማነሣሣት በሥርዓቱ ላይ የሚደረገውን ሠላማዊ ትግል ይበልጥ ለማቀጣጠልና ለማጠናከር እንጠቀምበታለን ።

4.3 አዲስ አበባ ከተማ የሀገራችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዎ ማዕከል እንደመሆንዋ መጠንም በአለው ብልሹ ሥርዓት ውስጥም ሆነን በመጭው አምስት አመት በቅንጅቱ መሪነት መልካም አስተዳደር በማስፈንና ከፍተኛ የልማት እድገት በተግባር በማምጣት ከተማዋን ጥሩ ሞዴል አድርገን በማሳየት በመጪው የአምስት ዓመት ምርጫ ሕዝብ ቅንጅቱን በሀገር ደረጃ ለመምረጥ ጉጉ ሆኖ እንዲጠብቅ ማድረግ እንችላለን። የውጪው ማህበረሰብም ከኢህአዴግ በተሻለ ቅንጅቱ ሀገሪቱን መምራት እንደሚችል በቂ እምነት እንዲያድርበትና ዲፕሎማሳዊ ድጋፍ እንዲሠጠን ማድረግ እንችላለን።

4.4 በፓርማ ውስጥ ባለን በቂ ውክልና ለውይይት የሚቀርቡ አጀንዳዎች የቅንጅቱ ተወካዬች ጥራትና ብቃት ያለው ሃሣብ እያቀረቡ እንዲከራከሩ በማድረግ ሕዝቡ ከገዥው ፓርቲ የተሻለ አማራጭ ፓሊሲና የሰው ኀይል ቅንጅቱ ያለው መሆኑን በእርግጠኝነት እንዲረዳ በማድረግ በአንድ በኩል የትግሉን ውጤት እያጣጣመ በዙሪያችን ተደራጅቶ እንዲታገል፤በሌላ በኩል ደግሞ በመጪው አምስት ዓመት ምርጫ እኛን ለመምረጥ ዝግጁ ሆኖ እንዲጠብቅ እናደርገዋለን።

ስለዚህ በምርጫው በምናገኛቸው ከላይ የተጠቀሱ ውጤቶች በአግባቡ እየተጠቀምንና በሀገር ደረጃ ጥራትና ብቃት ያለው ድርጅታዊ መዋቅር በመዘርጋት ከ5ዓመት በኂላ ያለጥርጥር መንግስታዊ ስልጣን የምንይዝበትን አስተማማኝ መሰረት እንጥላለን።

## 5. በዘንድሮ ምርጫ ከላይ የተጠቀሱትን ዉጤቶች ብናገኝ ገዥው ፓርቲ ሊከተል የሚችለው ስልት

ቅንጅቱ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ገዥው ፓርቲ ሁለት አይነት ስጋት ሊያድርበት ይችላል። የመጀመሪያው ቅንጅቱ የአዲስ አበባን ሕዝብ በማነሳሳት ከ5 ዓመት በኂላ ከሚካሔደው ምርጫ በፊት ሥልጣኔን ሊያናጋውና ሊቀማኝ ይችላል ብሎ ይሰጋል። ሁለተኛው ቅንጅቱ ያገኘውን ውጤቶች ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ተጠቅሞ ከ5 ዓመት በኂላ ሥልጣኔን ያሣጣኛል ብሎ ይሰጋል። ከዚህ ስጋት ለመዳን ሁለት አማራጭ ሊወስድ ይችላል። የመጀመሪያው የአዲስ አበባ ምክር ቤትን ለመበተን ባለው ስልጣን መሰረት ምክር ቤቱን በትኖ አዲስ አበባ በጊዜያዊ አስተዳደር ስር እንድትቀጥል ሊያደርግ ይችላል።

ሁለተኛው አማራጭ ቅንጅቱ አሁን ባለው የሀገሪቱ ህግና ስርአት እየተገዛ አዲስ አበባን እያስተዳደረ እንዲቀጥል ማድረግና ነገር ግን የተለያዩ መሰናክሎችን እየፈጠረ ቅንጁቱ አዲስ አበባን በአግባቡ እንዳያስተዳድር በማድረግ ብቃት የለሽ አስመስሎ በማቅረብ ፤ በአንፃሩ ደግሞ በሀገር ደረጃ ከፍተኛ ለውጦችን በማምጣትና የተሻለ ስራ በመስራት ከ5 ዓመት በኂላ በዲጋሚ ለመመረጥ ሊሞክር ይችላል።በእኔ እምነት ህወሀት/ኢህአዴግ ሁለተኛውን መንገድ ይመርጣል ብዬ እገምታለሁ። ምክንያቱም ገዥው ፓርቲ አዲስ አበባን በመነጠቁ ተደናግጦና መብቱን ያለ አግባብ ተጠቅሞ የቅንጁቱን የአዲስ አበባን ምክር ቤት ቢያፈርስ የበለጠ ችግር ይገጥመዋል። ምክንያቱም በሕዝብ ትክክለኛ ውክልና የተመሰረተን ተቃዋሚ ፓርቲ ምክር ቤት የራስን በተጭበረበረ ምርጫ የተቋቋመ ምክር ቤት እንደማፍረስ ቀላል ስላልሆነ ምክር ቤቱን መርጦ ካቋቋመው ሕዝብ የሚገጥመው ተቃውሞ ቀላል አይሆንም።

ሕዝቡ የሥርዓቱን ህልውና የሚፈታተን ተቃውሞ ሊያስነሣ ይችላል ተብሎ ባይጠበቅ እንኳ ሥርዓቱን እውቅና የመንፈግ ያህል የሚያደርስ አቋም ሊወስድና በእልህ ከቅንጅቱ ጎን ቆሞ ለመታገል ይወስናል። ቅንጅቱም የምክር ቤቱን መፍረስ እንደ አንድ የመታገያ አጀንዳ በመጠቀም ትግሉን ይበልጥ ለማፋፋም ሊጠቀምነት ይችላል። በሕዝብ የተመረጠው የቅንጅቱ ምክር ቤት መፍፈስ በዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ሊያስነሳም ይችላል። በእነዚህ ምክንያቶች ገዢው ፓርቲ በበተነው ምክር ቤት ምትክ ሌላ ምክር ቤት በምርጫ ለማቋቋም መሞከሩ አይቀርም። በዚህ አይነቱ የድጋሚ ምርጫ ደግሞ ዞሮ ዞሮ ቅንጅቱ የበለጠ የመመረጥ እድል ይኖረዋል። እንዲህ አይነቱ የፓለቲካ ውጣ ውረድም የሕዝብን ብሶት እየጨመረና ትግሉን የበለጠ እያጠናከረው ስለሚመጣ ገዥው ፓርቲ ከመጪው ምርጫ በፊት የህልውና አደጋ ሊያጋጥመው ይችላል። ስለዚህ እነዚህን ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ ገዥው ፓርቲ የቅንጅቱን ምክር ቤት ከማፍረስ ይልቅ ከላይ የተጠቀሰውን ሁለተኛ ስልት ይመርጣል ብዬ እገምታለሁ።

ኢህአዴግ ከሁለቱ አማራጮች ሁለተኛውን ስልት እንዲመርጥ በማድረግ እረገድም ቅንጅታችን የራሱን አስተዋፅኦ ሊጫወት ይችላል። ቅንጅቱ በምርጫው ባገኘው ድሎች ተመክቶና ስሜት ውስጥ ገብቶ የትግሉን እየተጠናከረ መምጣት በማየት ገዥው ፓርቲ ከመጪው ምርጫ በፊት ከስልጣን ለማውረድ ከሞከረ ሁለት አይነት አደጋዎችን ሊያስከትል ይችላል። የመጀመሪያው ገዥው ፓርቲ ህገ መንግስታዊ መብቱን ተጠቅሞ የቅንጅቱን የአዲስ አበባ ምክር ቤት እንዲያፈርስ ሰበብ የሚፈጥር ሲሆን ሁለተኛውና የከፋው አደጋ ገዥው ፓርቲ ስልጣኑን ከውድቀት ለማዳን በሚያደርገው መፍጨርጨር ሀገራችን ተገቢ ወዳልሆነ የአመፅ መድረክነት ልትቀየር ትችላለች። ይህም የዲሞክራሲ ሒደቱን ጭምር ያጨልመውና ከ5 ዓመት በኂላ ሕዝብ የስልጣን ባለቤት ለመሆን ያለውንም እድል ሊያጠፋው ይችላል።

ስለዚህ የቅንጅታችን ስልት መሆን ሚገባው በስራላይ ያለውን ህግና ስርአተት ሣይጥስ በሠላማዊ መንገድ ተጠቅሞና በአዲስ አበባ ምክር ቤት ህልውናውን አስጠብቆ እስከመጪው ምርጫ መድረስና ሥርአቱ በምርጫ ውድድር ማሸነፍ መሆን ይገባዋል ብዬ አምናለሁ።

## 6. ይህ ምርጫ ስትራቴጂ ተቀባይነት ካገኘ ቅንጅታችን ሊወስዳቸው የሚገቡ ቅድሚያ እርምጃወች

ቅንጅታችን በዘንድሮ ምርጫ የሚገኘው ውጤት ይህ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ እነዚህን ውጤቶች በአስተማማኝ ሁኔታ አስጠብቀን ምርጫውን ልናጠናቅቅ የምንችልበትን ስልት መቀየስ ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ። በእኔ ዕምነት ሁለት መመዘኛዎችን ማለትም፤

6.1 ከላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ልናሸነፍ የምንችልባቸውን ከ100 ያልበሰጡ የምርጫ ክልሎች በጥንቃቄ መርጦ በማወቅ፤

6.2 ከቦታወቹ በተጨማሪም በምርጫ ክልሉ የቀረበው እጩ አሸንፎ የፓርላማ አባል ቢሆን ሀላፊነቱን በአግባብ ለመወጣት የሚያስችለው ችሎታና ብቃት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ ለተመረጡ የምርጫ ክልሎች ወይም እጩዎች የተለየ በጀትና እገዛ እንዲደረግ መወሰን ያስፈልጋል።

በእኔ እምነት ቅንጅቱ ካለው አጠቃለይ የገንዘብ አቅም 50% ለእነዚህ ለተመረጡት እጩዎች ማዋልና የተለያዩ ተጨማሪ እገዛዎችንም ከሌሎቹ አካባቢዎች በላቀ መጠን ማድረግ ይገባዋል ብዬ አምናለሁ። ሌላው በጥንቃቄ ልናከታውነው የሚገባ ቁምነገር ከምርጫው በኋላ የሚገኘውን ውጤት ሕዝብ፤ ደጋፊዎቻችን፤ አባሎቻችንና እጩዎቻችን ያለምንም የሞራል ውድቀት እንደከፍተኛ ውጤት አምነው ሊቀበሉ የሚችሉበትን ቅድመ የፕሮፓጋንዳ ስራ በጥንቃቄ መስራት ነው።

የምርጫው ውጤት ምንም ይሁን ምን እስከምርጫው ድረስ በምናካሂደው የምርጫ ዘመቻ በርግጠኝነት ምርጫውን እንደምናሸንፍ አድረገን ሕዝብን መቀስቀስ አማራጭ የሌለው ስልት ነው። ይህ ስልት በምርጫው የምናገኘውን ውጤት የተሻለ ለማድረግ ከሚኖረው ሚና ባላነሰ የምርጫው ውጤት ማሸነፍ መሆን ካልቻለ የትግሉን ቀጣይ ትኩሳት ሊያቀዘቅዝ የሚችል ጉዳት ያስከትላል። ይህንን ጉዳት አስቀድሞ ለመከላከል ወይም ለመቀነስ ሁለት ስልቶችን መከተል ተገቢ ነው ብዬ አስባለሁ።

የመጀመሪያው ስልት ከአሁን ጀምሮ እስከምርጫው እለት ድረስ ገዥው ፓርቲ ከመራጮች ምዝገባ ጀምሮ እየፈጸቸው ያሉ የማጭበርበር ስልቶችና ተፅኖዎች በበቂ መረጃ በተደጋጋሚ ለሕዝብ እያጋለጡ ምርጫው ነፃና ፍትሐዊ እንዳልሆነ ከወዲሁ የተረጋገጠ መሆኑን ለሕዝብ ማስጨበጥ አስፈላጊ ነው። ይህንን እውነታ ሕዝብ፤ነፃ ታዛቢዎች፤ ደጋፊዎቻችንና አባሎቻችን በሚገባ እንዲገነዘቡት እያደረግን ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ሕዝብ በድፍረት ወጥቶ እስከመረጠን ድረስ በአፈናው ውስጥም አልፈን የማሸነፍ እድላችን ከፍተኛ እንደሆነ አድረገን ጠንካራ ቅስቀሳ እናደርጋለን። በተለይም የምርጫ ዘመቻውን መጠናቀቅ አስመልክቶ ሚያዚያ 29 ቀን በመስቀል አደባባይ በምናካሂደው ስብሰባ በብዙ መቶ ሺህ ዎች የሚቆጠር ሕዝብ እንዲወጣ ምድረግና ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት መልእክቶች በበቂ ሁኔታ ማስተላለፍ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል።

በምርጫው የመጨረሻ ቀን ኢህአዴግ የሚጠቀምባቸውን የማጭበርበር ስልቶች አስቀድሞ በመተንበይና እስከምርጫው እለት ድረስ የታዩትን የምርጫ ግድፈቶችን በሚገባ አጠናቅሮ በማዘጋጀት የምርጫው እለት አመሻሽ ላይ የድምፅ ቆጠራ ከመጠናቀቁ ቀደም ብሎ ምርጫው በከፍተኛ ምጭበርበርና አፈና የተሞላ እንደነበርና ውጤቱን የማንቀበለው መሆኑን የሚገልፅ ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት መቻል አስፈላጊ ይሆናል። በየምርጫ ጣቢያው በእለቱ ከተሰማሩት ታማኝ ታዛቢዎቻችን ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግም ኢህአዴግ በማጭበርበር ማሸነፉ እርግጠኛ ሆኖ በታየባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫው ውጤት ሰነድ ላይ ፊርማቸውን እንዳያስቀምጡ ማድረግ ተገቢ ነው። እነዚህንና እነዚህን መሰል እርምጃዎች በመውሰድ ውጤቱ እንደተጠበቀው ያልሆነው በሕዝ ድጋፍ ማጣት ሳይሆን በኢህአዴግ ማጭበርበር እና አፈና መሆኑን ምንም አይነት ብዝታ በማይፈጥር ሁኔታ ሕዝብን ማሳመን ያስፈልጋል። ሁለተኛው ስልት የምርጫው ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ከምርጫው እለት ቀድም ብሎ በየደረጃው የሚገኙ ዋና ዋና የፓርቲ አባሎቻችንና የፋይናስ ደጋፊዎቻችን የራሣቸውን ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ በሚገባ እንዲረዱትና የሥነ- ልቦና ዝግጅት እንዲያደርጉ ማድረግ ነው።

በአጠቃለይ ስልታችን ይህ መሆን ካልቻለ በዘንድሮው ምርጫ ልናገኝ የምንችለውን አነስተኛ ውጤትም ሣናገኝ ቀርተን እራሳችን በፈጠርነው የስልት ስህተት የትግሉንም ሆነ የህወሀት/ኢህአዴግ እድሜ ለሌላ 10 አመታት እንዳናራዝም ከፍተኛ ስጋት ያለኝ መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ